# ፍትህ ለአዲስ አበባ - የማህበራዊ ሚድያ ዘመቻ

በአዲስ አበባ የታየውን የመሬትና የኮንዶምንየም ምዝበራ በመቃወምና ፍትህ ለመጠየቅ የተዘጋጀ የማህበራዊ ሚድያ ዘመቻ።

በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ የነበረውን የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት በመቃወም ዜጎች ለአመታት ህዝባዊ አመፅ ሲቀጣጠል ነበር። በተለየ በኦሮምያና በአማራ ክልሎች ለፍትህ፣ ለእኩልነት እና ለፍትሃዊ ኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን የሚጠየቁ ሰላማዊ ሰልፎች ሲደረጉ ነበር። ይህን ተከትሎም በኢህአዴግ ሲመራ የነበረው መንግስት ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ አሰቃቂ እርምጃ ሲወስድ ነበር። ዜጎች ካለጥፋታቸው ታስረው ተሰቃየተዋል፣ ተገድለዋል እንዲሁም ከአገር እንዲሰደዱ ተገደዋል።

በ2010 ዓ.ም ኢህአዴግ ያካሄደው ግምገማ ተከትሎ ዶ/ር ዓብይ አህመድ የፓርቲው ሊቀመንበርና ጠቅላይ ሚንስተር ተደርገው መመረጣቸው ይታወሳል። ዶር ዓብይ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ የፖለቲካ መህዳሩን ለማስፋት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል። አገር ውስጥ በሽብርተኝነት የተፈረጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደ አገር ውስጥ ገብተው በሰላማዊ መንገድ አንዲንቀሳቀሱ በመፍቀድ የፖለቲካ ምህዳሩን የማስፋት ስራ ተሰርቷል።

ሌላው በዶር ዓብይ የተወሰደ እርምጃ የአዲስ አበባ አስተዳደርን አፍርሶ በአዲስ መልክ መዋቀር ነበር። በዚህም መሰረት የቀድሞው የሱሉልታና የሆለታ ከተሞች ከንቲባ የነበሩት አቶ ታከለ ኡማ በምክትል ከንቲባ ማእረግ የአዲስ አበባን አስተዳደር ሆነው ተሹመው ላለፉት ሁለት አመታት ሲሰሩ ቆየተዋል።

በአቶ ታከለ አስተዳደር ዘመን በአዲስ አበባ የታለያዩ አድሎአዊ አሰራሮች፣ ጥቅመኝነት፣ የህዝብን ሃብት ማባከን የመሳሰሰት ግድፈቶች ተስተውለዋል። ከነዚህም ግድፈቶች ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀሰው የመሬት ወረራና ፍትሃዊ ያልሆነ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እደላ ናቸው። እንዚህን ግድፈቶች አውጥጠው ሲቃወሙ የነበሩ የሰብአዊ መብት አራማጆች የተለያዩ ማስፈራሪዮዎች እና እስር ሲደርስባቸው አየተናል። የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) በቅርቡ ይፋ ያደረገው ጥናትም ይህንን የሚያረጋግጥ ሆኗል። ኢዜማ በጥናቱ ከ250ሺ ካሬ በላይ መሬት በህገወጥ መንገድ ወረራ የተያዘ ሲሆን፣ ከብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባለተገባ መንገድ ለግለሰቦች መተላለፋቸውን ያሳያል።

በአዲስ አበባ የሚስተዋለውን የነዋሪዎች ቤት አልባነት ለመቅረፍ ከ1997 ጀምሮ ተመዝግበው በየወሩ ሲቆጥቡ የነበሩ የነበሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ቤት ሳየገኙ ቀርተው ኢፍትሃዊ በሆነ አሰራር በቆጠቡት ገንዘብ የተሰራውን የጋራ መኖሪያ ቤት ላልተመዘገቡና ላልቆጠቡ ግለሰቦች መዘዋወራቸው ቁጣን ቀስቅሷል። ይህንን በመቃው የታየው አይን ያወጣ ሙስናና ምዝበራ እርምት እንዲወሰድበት፣ አጥፊዎች አንዲጠየቁ እንዲሁም ፍትህ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች የሚጠይቅ የማህበራዊ የተቀናጀ ዘመቻ ተዘጋግቷል።

## የዘመቻው አላማ

1. የአዲስ አበባን ህግ ወጥ የመሬት ወረራና እና የኮንዶሚኒየም እደላ በተመለከተ ጥያቄዎችን ማንሳት እና ፍትህ መጠየቅ!

2. በተለያዩ ሚዲያዎች ሲነገር የነበረው ወንጀል እና ጥልቅ ምርመራ የተደረገበት ጉዳይ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ (በጠቅላይ አቃቤ ህግ) እንዲያዝ መጠየቅ

3. እንዲሁም በህገ-ወጥ ተግባር ላይ ተሰማርተዉ የተገኙ ግለሰቦች በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ማሳሰብ፡፡ በዚሁ ሰበብ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንደ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ እንባ ጠባዊ ተቋም እና ሌሎች የሰብአዊ ድርጅቶች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የምርመራ ሪፖርት ይፋ እንዲያደርጉና አጥፊዎች ለህግ እንዲቀርቡ ጫና እንዲዮደርጉ መጠየቅ።

## **Justice for Addis Abeba:** *A Social Media Campaign*

A social media campaign designed to push back against and ask about the land and condominium theft going on in Addis Abeba.

Ethiopians have been protesting human and democratic right infringements for years now. People have raised questions concerning justice, equality and a just economic participation especially in the Oromia and Amhara regions. The EPRDF government had been using brutal means of subduing these protestors. Citizens were arrested without reason, killed and exiled.

Recall that Dr Abiy Ahmed was elected as leader after the in-party discussions of 2018. And since his rise to power, Dr Abiy has tried to widen the political space. They allowed previously exiled political parties to re-enter Ethiopia so they can join the political space and work in a peaceful struggle.

Another step that was taken by Dr Abiy is the reshuffling of Addis Abeba's administration. Accordingly, the mayor of Sululta and Holeta Takele Uma was made the deputy mayor of Addis Abeba for the past two years.

Under Takele Uma's administration, Addis Abeba saw unfair treatment, waste of people's resources and privilege to some groups. The main issue however remains the unjust distribution of land and condominiums. We have watched as individuals advocating against this face threats and imprisonment. EZEMA has just recently released a study confirming this. EZEMA has stated that over 250,000 square kilometres of land has been illegally taken and that over thousands of condominium houses have been given to individuals illegally.

People have been angered at the fact that the houses were built by money saved by Addis Abeba's residents since 2005 but was given to individuals outside this group. This campaign is organised so that the corruptions is fixed, the officials be asked accordingly and that Addis Abeba's residents are given justice.

**The aims of this campaign:**

1. To raise questions about Addis Abeba's illegal land and condominium house allocations

2. To ask the court of the Attorney General of the country to take this up and conduct in-depth investigations

3. To demand that those involved be asked according to the law. It is also to pressure the Ethiopian Human Rights Commission, the Ombudsman and other human rights organisations to focus on this issue so the culprits are brought to justice